# ፈጥነህ ርስትህን ውረስ

## የኢያሱ

“…አንተ ሸመገልህ በዕድሜህም አረጀህ፤ ያልተወረሰች እጅግ ብዙ ምድር ገና ቀርታለች፤ …” ኢያሱ 13፥1

የጽዮን ክብር ቤተ ክርስቲያን ቫንኩቨር፤ ካናዳ

2/13/2009

# ጥናት አንድ

ከዛሬ ጀምሮ በተካታታይ የኢያሱን መጽሐፍ መሠረት በማድረግ 12 ጥናቶችን እናጠናለን።

**ንዑስ ርዕስ፥ አትፍራ እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ**

**»@ያሱ 1፣1-10**

**ዓላማ፥**

(ለመሪው ብቻ) አማኝ በሕይወቱ መከናወንን እንዲያገኝና አስፈሪውን ሁኔታ ለማለፍ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝና እርሱን በመታመን መኖር እንዳለበት ለማስገንዘብ

**መግቢያ፥**

በሙሴ ምትክ የመሪነቱን ሥፍራ ለያዘው ለኢያሱ ሕዝቡን በመምራት እግዚአብሔር ወደ ሰጣቸው ምድር ለማድረስ እንዲችል ምን ማድረግ እንደሚገባው እግዚአብሔር ያዘዘውን እንመለከታለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. ከሙሴ ሞት በኂላ እግዚአብሔር ለኢያሱ እሱና ሕዝቡ ምን እንዲያደርጉ ያዛል?
2. ከፊት ለፊታቸው ያለውን ዮርዳኖስን ተሻገሩ ብሎ ሲያዛቸው ከቀደመው ታሪካቸው በልባቸው ምን ሊያስቡ ይችላሉ ትላለህ?
3. “የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠውን ስፍራ ሁሉ ለእናንተ ሰጥቻለሁ” ለምን አለ?
4. እግዚአብሔር ለኢያሱ ለግሉ ምን ይለዋል?
    - “በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም” ሲል ለአዲሱ መሪ ለኢያሱ ምን ትርጉም አለው?
5. ማንም ሊቋቋመው የማይችለው ከምን የተነሳ ነው?
6. ኢያሱ ለሕዝቡ አለቆች ምን ይላቸዋል? ለቀሩት ሁለት ተኩል ነገዶችስ ምን ይላል? ለንግግሩስ ምን መለሱለት?
    - ይህ መልሳቸው ócቶ ለነበረው ኢያሱና ለተቀበለው ኃላፊነት ምን አስተዋፅዖ አለው?
7. ስለነገ ስታስብና ስትፈራ ይህን ለማሸነፍ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር እንደሆን የቱን ያህል ከልብህ ትፈልገዋለህ?
    - በህይወትህ እንድታድግና ፍሬህም የበዛ እንዲሆን ምን ማድረግ ያለብህ ይመስልኃል?

# ጥናት ሁለት

## ን—ስ ርዕስ፥ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ክንውን ጅማሬ

## ኢያሱ2፥1-24

ዓላማ፥

አማኝ በእግዚአብሔር ፈቃድ በሚሄድበት በማን ውም ሥፍራ የእግዚአብሔርን ማከናወን እንደሚያገኝ ለማስገንዘብ

መግቢያ፥

ኢያሱ ኢያሪኮን ይሰልሉ ዘንድ የላካቸው ሰዎች ያጋጠማቸውንና ያመጡትን ወሬ አብረን እንመለከታለን።

ጥያቄዎች

1. በሚስጥር ሊሰልሉ የተላኩ ሰዎች ኢያሪኮ ከገቡ በኋላ ወዴት ሲያቀኑ ይታያል? እንዴት ወድዚች ጋለሞታ ሊገቡ ቻሉ ትላለህ?
2. ሰላዮች ወደ ምድሪቱን መግባታቸውን የሰማው የኢያሪኮ ንጉስ ምን ሲያደርግ ታያል?
    - ጋለሞታይቱ ረዓብ ምን ትመልስላቸዋለች?
3. አሳዳጆች ከሄዱ በኋላ ለሰላዮች ምን አላቸው?
    - ከንግግሯ ስለ ሴትየዋ ምን ትረዳለህ?
    - አዳማጮቹስ ከዚህ የተነሳ ምን ይሰማቸዋል ትላለህ?
4. ለንግግሯ ምን መልስ ይሰጣሉ? /ቁ.14-22/
    - እግዚአብሔር ሊያጠፋት ካለው ከተማ ይህች ጋለሞታ ሴት ለማዳንዋ የሚሆንን ነገር ማግኘቷን ስታይ ስለ እግዚአብሔር ምን ትረዳለህ?
5. ሰዎች ወደ ኢያሱ በመጡ ጊዜ ምን ራፖር (ሪፖርት ዘገባ) አቀረቡ?
    - እንዴትስ ይህን ሊሉ ቻሉ ትላለህ?
6. እግዚአብሔር በምዕራፍ 1 ለኢያሱ ከአንተ ጋር እሆናለሁ ያለውን እንዴት እንዳጸናው አየህ?

ተዛምዶ፥

- አማኝ ከእግዚአብሔር ተስፋን ከተቀበለና በፈቃዱ ከሄደ እግዚአብሔር ራሱ እንደሚያከናውንለት ምን ያህል ከዚህ ክፍል ተረዳህ?
- እግዚአብሔር ለፍርድ ከወሰነባት ከተማ አንዲትን ጋNY ታ† ቤተሰቧን ማትረፉን ስታይ ስል እግዚአብሔር ምህረት ምን ትላለህ?
- እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ከሆነ ጠላት በፊትህ ሊቆም እንደማይችል/ልቡ እንደሚቀልጥ/ የቱን ያህል ታምናለህ? ሌላስ ምን አስተዋልክ?

# ጥናት ሦስት

## ን–ኳ ርዕስ፥ እስራኤል በእግዚአብሔር ድንቅ ዮርዳኖስን ተሻገሩ

ዓላማ፥

አማኝ በሕይወት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚራመድበት ጊዜ በመንገዱ የሚገጥመውን ማንኛውንም መሰናክል በተዓምር ሊያሻግረው እንደሚችል ለማሣየት

መግቢያ፥

በዮርዳኖስ ዳር የነበሩት የእስራኤል ሕዝብ ወንዙን እንዴት እንደተሻገሩ በዛሬው ጥናታችን እናያለን።

ጥያቄዎች፥

1. የእሥራኤል ሕዝብ ከሰጢም ወደ ዮርዳኖስ ከመጡ በኋላ የህዝቡ አለቆች ህዝቡን ምን ሲያዙ ይታያል?
2. ኢያሱ ለሕዝቡ እንዲሁም ለካህናቱ ምን አላቸው?
   - እግዚአብሔር በእሥራኤል ፊት ድንቅ ነገር እንዲያደርግ ሕዝቡ ምን ማድረግ አለበት? ከዚህስ ምን ትማራለህ?
3. በዚህ የዝግጅት ጊዜ የእግዚአብሔር መልዕክት ምን ነበር?
   - ይህ መልእክት በኢያሱ ልብ ውስጥ የሚፈጥረው ነገር ምንድነው?
4. ከቁጥር 9-13 ባለው ክፍል ውስጥ ኢያሱ ለሕዝቡ ምን ሲላቸው ትመለከታለህ?
5. ኢያሱ ዮርዳኖስ ወንዝ ተቋርጦ ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ እንድ ክምር ሆኖ ይቆማል ብሎ ሲናገር በእግዚአብሔር ላይ ስላለው እምነት ምን ታያለህ?
6. የቃል ኪዳኑ ታቦት የተሸከሙት ካህናት እግሮች በውሃው ዳር ሲጠልቁ የሆነውን ነገር ዘርዝር።
   - በእስራዔል ሕዝብ የጉዞ ታሪክ ውስጥ ይህ ተዓምችት ለሁለተ ጊዜ መፈሙ ሕዝቡ ስለ እግዚአብሔር ምን አመለካከት እንዲኖረው ያደርጋል?
   - በቁጥር 10 ባለው ሃሳብ መሠረት የኣሁኑ ዮርዳኖስ መሻገራቸውን ለወደፊት ላለው ሰልፍ ምን ዋስትና ይሰጣቸዋል?

ተዛምዶ፥

- አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ሲሆን የት ውም ዓይነት ሁኔታን ማለፍ እንደምትችል የቱን ያህል አስተዋልክ?
- እግዚአብሔር ለሕይወትህ ድንቅና ተምራት እያደረገ እንዲመራህ የአንተ በእርሱ ፊት ሁልግዜ በቅድስና መገመት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አስተዋልክ?
- ከዚህ ክፍል ሌላ ያስተዋልከው ካለ አካፍል።

## ጥናት አራት

### ርዕስ፥ ነውርን ማስወገድ ኢያሱ 5፥1-9

**ዓላማ፥**

እግዚአብሔር በሕይወታችው ውስጥ ተመልክቶ እንድናስወግደው የተናገረንን ነውር ፈጥነን በማስወገድ በንፅሕና ከእግዚአብሔር ጋር መጓዝ እንዳለብን ለማሳየት

**መግቢያ፥**

የእስራኤል ልጆች ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ የአህዛብ መንግስታት እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚፈልገው ነገር ምን እንደሆነና የእስራኤልም ልጆች ምላሽ ምን እንደነበር እንመለከታለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. የእስራኤል ልጆች ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ የአህዛብ ነገስታት ምን ሲሆኑ እናያለን?
    - የአሞራውያንና የከነዓውያን ነገሥታት ልባቸው ለምን ቀለጠ? /ቁ.1/ ከዚህስ ምን ታስተውላለህ?
2. እግዚአብሔር ኢያሱን ምን ሲያዘው ይታያል? ኢያሱስ ምን አደረገ?
3. እግዚአብሔር ኢያሱን የእስራኤልን ልጆች “ሁለተ ግዜ ግረዛቸው” ሲል (ቁ.2) ምን ማለቱ ነው? ለምንስ አስፈለገ? (ቁ.2,4)
4. የእስራኤል ልጆች ከተገረዙ በኋላ ምን አደረጉ?
5. በቁጥር 9 ላይ እግዚአብሔር ለኢያሱ ምን ሲለው ይታያል?
6. “ዛሬ የግብጽን ነውር ከአንተ ላይ አንከባልያለሁ” ከሚለው አባባል ስለ ሰው ድርሻና ስለ እግዚአብሔር አሰራር ምን ትረዳለህ?
7. እግዚአብሔር የሚያሳይህን ነውር ከሕይወትህ ካላስወገድህ ከእግዚአብሔርም ጋር ሆነ ከህዝቡ ጋር ህብረት ተካፋይ ሆኖ መጓዝ እንደማይቻል አስተዋልክ?

**ተዛምዶ፥**

ከክፍሉ ሌላ ያስተዋልከው ነገር ካለ ለሌሎች አካፍል።

# ጥናት 5

## ን–ቫ ርዕስ፡ በእምነት በመታዘዝ የሚገኝ ድል

**(ኢያሱ5፡13-6፡24)**

**ዓላማ፡**

የእግዚአብሔር አሠራር እንደ ሰው አስተሳሰብ ባይሆንም ድል የሚገኘው በሞኝነትና በጥንቃቄ በመታዘዝ መሆኑን ለማሳየት።

**መግቢያ፥**

የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔር የኢያሪኮን ግንብ እንዲዞሩ ሲያዛቸው በእምነት ወጥተው እንዴት ድል እንዳገኙ እናያለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. ×ምዕራፍ 5፡13-15 ምን ትመለከታለህ? “የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ” መገለጡ ወደፊት ጦርነት ለሚጠብቃቸው ለኢያሱና ለሕዝቡ ምን አስተዋፅዖ የሚኖረው ይመስልሃል?
2. እግዚአብሔር ለኢያሱ ምን ሲናገረው እናያለን?
   - ኢያሱ እግዚአብሔር ያዘዘውን ለሕዝቡ ከገለ በኂላ ኢያሪኮን ከመውረሳቸው በፊት ምን ማስጠንቀቂያ ሰጣቸው?
   - ሰባት ግዜ ከዞሩስ በኂላ ምን ምን እንዳያደርጉ ከለከላቸው? (ቁ.17-19) እርም ከሆነው ነገር ራሳችሁን ጠብቁ ያላቸው ለምንድነው?
3. የእሥራኤል ልጆች በአንድ ቀን ሰባት ጊዜ ከመዞር ይልቅ በየቀኑ አንድ ጊዜ እየዞሩ ከሰባት ቀን በኂላ በጩኸት ድል ማግኘታቸው ስለ እግዚአብሔር አሠራር ምን የሚያስተምረው ይመስልሃል?
   - ጋለሞታይቱ ረዓብ ከጥፋት መዳንዋን ስትመለከት ከዚህ ምን ትማራለህ?
   - እስራኤል ኢያሪኮን ከማረኩበት የውጊያ ስልት ያገ ከውን ትምህርት ምንድነው ነው?

**ተዛምዶ፥**

- ለሰው ሞኝነት የሚምመስለው የእምነት አሠራር በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል ዋጋ እንዳለው አስተውለሃል?
- የአእምሮ እውቀትህን ጥለህ በሞኝነት ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ተዘጋጅተሃል?
- ሌላ ከክፍሉ የተማርከውን ካለ ለሌሎች አካፍል።

# ጥናት 6

ንዑስ ርዕስ ፥ ስውር በደል የሚያስከትለው ሽንፈት(ኢያሱ7፡1-26)

ዓላማ ፥

በአማኝ ያለው የተሰወረ ኃጢአት ለራሱና ለቤተክርስቲያን ለሽንፈት ሊያደርግ እንደሚችልና በዚህም በአማኝ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ሊገለጥ እንደሚችል ማሳየት

መግቢያ ፥

አካን በተሰወር ኃጢአት የእስራኤልን ማህበር እንዳስጨነቀና በመጨረሻ እርሱ ራሱ በበደሉ ምክንያት ከነቤተሰቡ እንዴት እንደጠፉ እናያለን፤

## ጥያቄዎች

1. ቁ. 2-5 ላይ ምን ትመለከታለህ?
2. ለጊዜው ለገጠማቸው ሽንፈት ኢያሱ ምን ሲያደርግ ታያለህ?
   - ኢያሱ ከቀረበበት ሁኔታ ሲታይ ለሽንፈት ጊዜ ስለ መቅረብ ፡ሎት ምን ትረዳለህ?
3. ለኢያሱ ጸሎት የእግዚአብሔር ምላሽ ምን ነበር? (10-15)
   - ቃል ኪዳንን ማፍረስ በዚህ ዘመን ምን የሚያስከትል ይመስልኃል? (11-12)
4. እግዚአብሔር እርሙ የተገኘበት ሰው እርሱና ያለው ሁሉ በእሳት ይቃጠላል ሲል (ቁ. 15) ስለ ፍርዱ ምን ታስተውላለህ?
5. ኢያሱ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ምን ሲያደርግ ይታያል? (16-21)
   - አካንን ወደ አለመታዘዝ የመራው መሠረታዊ ነገር ምን ይመስልሃል? (ቁ.21)
6. አካን የደበቀው እርም ከተገኘ በኂላ ኢያሱ ምን እርምጃ ሲወስድ ታያለህ? (22-25)
   - የአንድ ሰው ስውር በደል እንደ ማህበሩ በደል ተቆጥሮአልና (1-12) ይህ ለምን የሆነ ይመስልሃል?

## ማዛመድ፥

- ድንገተኛ መነሻውን ያላወቅከው ውድቀት ቢደርስብህ እንደ ኢያሱ በእግዚአብሔር ፊት በመደፋት መፍትሄ እንደሚገኝ አስተውለህ ተለማምደሃል?
- ስውር በደልን በግል መለማመድ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚጎዳና አንተም በመጨረሻም እንደሚያጠፋ አስተውለሃል?
- እግዚአብሔር በፍርዱ ጨካኝ መሆኑን ተረድተህ እርሱን በመፍራት ትኖራለህ? ከክፍሉ ሌላ ምን አስተዋልክ?

# ጥናት 7

ርዕስ፥ እንዳትታለል እግዚአብሔር ጠይቅ (ኢ.ያሱ 9፥1-27)

ዓላማ፥

ጠላት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ተዋግቶ ማሸነፍ እንደማይችል ሲያውቅ በማታለል በድርድር ከዚህ ቅዱስ ህዝብ ጋር ተመሳስሎ በመኖር በቁጥጥር ስር ለማድረግ ስለሚፈልግ በማንኛውም ነገር የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመጠየቅና በመረዳት መኖር እንዳለበት ለማሳየት።

መግቢያ፥

የኤዋውያን ወገኖች የሆኑት የገባዖን ሰዎች በተንኮል ኢያሱን እንዴት እንዳታለሉት በዚህ ጥናታችን እንመለከታለን።

ጥያቄዎች፥

1. ኃይላቸውን አስተባብረው በኢያሱና በእስራኤላውያን ለመዝመት የመጡት እነማን ናቸው?
2. የገባኦን ሰዎች ወደ ኢያሱ ለመሄድ ያደረጉት ዝግጅት ምን ይመስል ነበር?
   - አሁን ከእኛ ጋር ኪዳን አድርጉ አሉ ከሚለው ሃሳብ ትረዳለህ? ኪዳን ከሚለው ሃሳብ ምን ትረዳለህ? ኪዳን ማድረግ የፈለጉት ለምንድነው?
3. ከቁጥር. 7-15 ባለው ክፍል ውስጥ እንደተመለከተው የገባዖን ሰዎች ኢያሱን ያታለሉት እንዴት ነበር?
   - ከዚህ ሁኔታ ስለ ጠላት አሠራር ምን ትረዳለህ?
4. በቁጥር 14 ላይ የእሥራኤል ሰዎች ምን አይነት እርምጃ ወሰዱ?
   - ለጠላት የተንኮል አቀራረብ ኢያሱና እስራኤላውያን ምን አይነት ምላሽ ሊኖራቸው ይገባ ነበር?
5. የገባኦን ሰዎች እውነተ  ማንነት እንዴት ነበር? (ቁ.16)
6. በሰልፍ ሜዳም ይሁን በሌላ ሁኔታ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይጠይቁ እርምጃ መውሰድ ምን ያስከትላል ትላለህ? (ቁ.18)
   - የማህበሩ አለቆች የማህበሩን /የሕዝቡን/ ማጉረምረም እንዴት አስተናገዱት?
   - በሰልፍ ሜዳ /በውጊያ ላይ/ ይህ የሕዝብ ማጉረምረም ቢበረታ ኖሮ ውጤቱ  ምን ይሆን ነበር?
7. ኢያሱ የገባያንን ሰዎች ጠርቶ ምን ብሎ ጠየቃቸው?
   - የእነርሱስ መልስ ምን ነበር?
   - ሰልፍ ወይም ውጊያ የሚለውን ሃሳብ እንዴት ትረዳዋለህ?
   - የእግዝሐብሔር ፈቃድ ማወቅ ከውጊያ ሕይወት ጋር እንዴት ታያይዘዋለህ?

ተዛምዶ፥

- በህይወት ጉዞ ውስጥ በማን ውም አቅጣጫ እግዚአብሔር አምላክህን ለማንኛውም ነገር መጠየቅና ፈቃዱ ማወቅ እንዳለብህ ምን ያህል ተረዳህ? በነገር ሁሉ የጠላትን የረቀቀ ሃስብ በማስተዋል ሃሳቡን ለማፍረስ ምን ያህል ንቁ ነህ?

# ጥናት 8

## ንዑስ ርዕስ፥ የእስራኤል ጠላቶች በገባዖን ተመቱ።

**(ኢያሱ 10፥1-15)**

**ዓላማ፥**

በእሥራኤል ላይ በማበር የተነሱትን የጠላት መንግስታትን ሠራዊት እግዚአብሔር እንዴት በድንቅ እንደመታቸው ለማሳየት

**መግቢያ፥**

አምስቱ የአሞራውያን ነገስታት ከእስራኤል ጋር በተዋጉ ጊዜ የተፈጸመውን እንመለከታለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. የኢየሩሳሌም ንጉስ ስለ ኢያሱ ምን ሰማ? የሰማውስ ነገር ምን ስሜት ፈጠረበት?
2. አምስቱ የአሞራውያን ነገስታት ገባዖንን ለመምታት በወጡ ጊዜ ኢያሱ ለእርዳታ ሲጠየቅ ምን አደረገ? እግዚአብሔርስ ምን አለው?
3. ኢያሱ በጦርነት ስፍራ ደርሶ ውጊያ ከመጀመሩ በፊት እግዚአብሔር ምን አደረገ?
   - ከዚህ ስለ እግዚአብሔር አሠራር ምን ትማራለህ?
   - እግዚአብሔር በበረዶ ናዳ መዋጋቱን ስትመለከት ስለ እግዚአብሔር ምን ትላለህ?
4. የፀሃይ መቆምና የጨረቃ መዘግየት ስትመለከት እንደዚሁ የአምስቱ የአሞራውያን ነገስታት በአንድ ጊዜ ተሰባስበው በአመቺ ሁኔታ በኢያሱ እጅ መውደቅ በቁጥር 8 ካለው ሃሳብ ጋር እንዴት ታያይዘዋለህ?
5. የፀሃይ መቆምና የጨረቃን መዘግየት ስትመለከት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ የእምነት ሎት ምን ትረዳለህ?

**ተዛምዶ፥**

6. ተስፋን የሰጠው እግዚአብሔር ለኢያሱና ለእስራኤቆቅ ጠላቶቻቸውን በመምታት ድልን ሊሰጣቸው ስታይ ልብህ ምን ያህል በእግዚአብሔር ይታመናል?
7. ጨርሶ ባልተለመደና ተዓምራዊ በሆነ መንገድ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደተዋጋ እንደዚሁ ዛሬ ለአንተና ለአማኞች በሙሉ በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔር ሊዋጋ እንደሚችል አስተዋልክ?

# ጥናት

## ንዐሰ ርዕስ፤ ተስፋን ለመውረስ በጽናት መውጣት

**ኢያሱ 13፥1-7፤ 14፥1-15**

**ዓላማ፥**

እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ሳይሞላ እንደማይተውና ሰው ደግሞ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ለመውረስ በጽናት መውጣት እንዳለበት ለማሳየት።

**መግቢያ፥**

ገና ሣይወርሱ ስለቀረው ምድር እግዚአብሔር ለኢያሱ የተናገረውንና ካሌብ ደግሞ ስለተገባለት የተስፋ ቃል የጠየቀውንና የተመለከተው እናያለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. በምዕራፍ 13 መጀመሪያ ላይ እግዚአብሔር ኢያሱን ምን ይለዋል?
2. በኢያሱ 14 ውስጥ ካሌብ ለኢያሱ ምን አለው?
3. ካሌብ እኔ ግን አምላኬን እግዚአብሔርን ፈጽሜ ተከተልኩ (ቁ.8) ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ካሌብ ፈጽሞ እግዚአብሔርን በመከተሉ ከእግዚአብሔር በሙሴ በኩል የተሰጠው ተስፋ ምን ነበር?
5. እግዚአብሔርን ፈጽሞ መከተል ተስፋ መውረስ እንዴት ይያያዛሉ?
6. ኢያሱ የካሌብን ጥያቄ እንዴት አስተናገደ?
7. ካሌብ በተሰጠው ተስፋ መሠረት ሳይጠይቅና በእምነት ባይወጣ ምን ሊሆን ይችላል ብለህ ታስባለህ?

**ተዛምዶ፥**

1. ኢያሱ ቢሸመግልም ገና ብዙ ያልተወረሰ ምድር እንደነበረው ሁሉ አንተም እግዚአብሄር ለአንተ በክርስቶስ በኩል ያዘጋጀው ብዙ በረከት እንዳለ ምን ያህል ትተጋለህ?
2. በተስፋው ቃል ላይ በመቆም ድርሻውን ስለአገኘው ካሌብ ስትመለከት አንተስ ተስፋህን ለመጠበቅና ለመጠየቅ ምን ያህል ትበረታለህ?

## ጥናት 10

**ንኡሰ ርዕስ፥ በእግዚአብሔር ተዋጊነትና በመታዘዝ ርስትን መውረስ**

**ኢያሱ 23፥1-16**

**ዓላማ፥**

እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ የሚዋጋ ብርቱና ኃያል አማላክ እንደሆነና ሕዝቡም በሙላት ርስትን ለመውረስ በመታዘዝ መኖር እንዳለበት ለማስገንዘብ።

**መግቢያ፥**

ኢያሱ በሸመገለና በእድሜው ባረጀ ጊዜ እስራኤልን ሁሉ ሽማግሌዎቻቸውንም አለቆቻቸውንም ፈራጆቻቸውንም ሹማምንቶቻቸውንም ጠርቶ የተናገራቸውን እንመለከታለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. ከብዙ ዘመን የሰልፍ ጉዞ በኂላ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገላቸው ምንድን ነው?
2. በቁ. 3 ኢያሱ ለእስራኤል በሙሉ ምን ሲላቸው እንመለከታለን?
   - ስለ እስራኤል የተዋጋ አምላካቸው እግዚአብሔር መሆኑ ለእነርሱ ምን ውጤት አመጣላቸው?
3. እስራኤል ለወደፊት በሚኖሩት የህይወት ዘመናቸው ሁሉ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ይመክራቸዋል? (ቁ.6-11)
4. “ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ተጠጉ የሚለውን አባባል እንዴት ትረዳዋለህ? ይህንንስ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል?
5. እግዚአብሔር እጅግ ታላላቅና ኀይለኞች የሆኑትን አህዛብ ከፊታቸው ማስወጣቱና እስራኤልን ማንም ሊቋቋመው አለመቻሉን ስትመለከት ስለ እግዚአብሔር ምን ትረዳለህ?
6. እስራኤላውያን ከአህዛብ ጋር ቢወዳጁ ቢጋቡ ወደ እነርሱም ቢጠጉና ሌሎችንም አማልክት ቢያመልኩ ውጤቱ ምን ይሆናል?
   - ከዚህስ ስለ እግዚአብሔር አሠራር ምን ትረዳለህ?

**ተዛምዶ፥**

7. እግዚአብሄር ስለ ሕዝቡ የሚዋጋ ብርቱ ጦረ እንደሆነ ስትመለከት አንተም በምትኀዝብት የሕይወት ውጣ ውረድ ሁሉ ስለ አንተ እየተዋጋ በድል ሊመራህ ርስትን ሊያወርስህና ሊያስርፍህ እንደሚችል ምን ያህል በዚህ አምላክህ ልብህ ምን ያህል አርፏል?
8. አምላክህ የገባህልን ተስፋ በድል መውረስና ማፅናት እንድትችል ወደ አምላክህ እጅግ መጠጋት መውደድና ሙሉ ለሙሉ ራስህን በመስጠት በትዕዛዙ መሄድ እንዳለብህ አስተውለሃል? ከክፍሉ ሌላ ምን አስተዋልክ?

# ጥናት 11

## ንኡስ ርዕስ፥ እግዚአብሔርን ለማምለክ መወሰን

### ኢያሱ 24፥1-28

**ዓላማ፥**

እግዚአብሒር ለእርሱ የተዋጋበት ጠላቱንም በእጁ አሳልፎ በመስጠት ርስትን እንዲወርስ የመራው ሕዝብ እግዚአብሔር አምላኩን በእውነት ማምለክና ትዕዛዙንም መጠበቅ እንዳለበት ለማሳየት።

**መግቢያ፥**

በዚህ ጥናት ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የተናገራቸውን ኢያሱምየመከራቸውንና የሕዝቡን ምላሽ እንመለከታለን።

**ጥያቄዎች፥**

1. ኢያሱ የእስራኤል ሕዝብ ሽማግሌዎችን አለቆቻቸውን ፈራጆቻቸውንና ሹማንምቶቻቸውን ሲጠራቸው እነርሱስ ምን አደረጉ?
2. እግዚአብሔር ለእስራኤል ህዝብ ያደርገላቸውን በአጭሩ ዘርዝር (ቁ.2-13)
3. የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ በማን የተሠራ ነው? ከዚህስ ለእግዚአብሔርና በህዝቡ መካከል ስላለው ግንኙነት ምን ትረዳለህ?
4. ኢያሱ ለእስራኤል ህዝብ ምን ሲመክራቸው ትመለከታለህ? (ቁ.14-15)
   - o የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ" እና "እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን" የሚሉትን ሃሳቦች አብራራ
5. ኢያሱ ለመከራቸው ምክር ምላሽ ምን ነበር?
   - o "እርሱ አምላካችን ነውና እግዚአብሄርን እናመልካለን" ብለው ለመወሰን ያበቃቸው ሁኔታ ምንድን ነው?
6. በቁ.19-20 ኢያሱ የተናገረውን ሃሳብ እንዴት ትረዳዋለህ?
7. እግዚአብሔር አምላካቸውን እንደሚገባ ለማምለክ ህዝቡ ማድረግ ያለባቸው ምንድን ነው? (ቁ.23)
8. ኢያሱ ወደ ሞት በቀረበ ጊዜ እንኳ ለህዝቡ የመከራቸውን ፅኑ ምክር ስትመለከትና ለመጨረሻውም ሥርዓትና ፍርድን እንዳደረገላቸው ስታይ ስለ እውነተኛ መሪ ምን ትገነዘባለህ?

**ተዛምዶ፥**

9. እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከኃጢአት ባርነት ነጻ አውጥቶ የተባረከ ተስፋውን በመንፈስ ቅዱስ አማክይነት እንድወርስ ሲያደርግ አሁንስ እርሱን ለማምለክ ልብህ ምን ያህል የጨከነ ነው?
   - o የምትመራቸው ሰዎች እግዚአብሔር ያዘጋጃላቸውን የህይወት ባለጠግነት እንዲወርሱና እርሱን በህይወታቸው ዘመን ሁሉ እንዲያመልኩትና እንዲታዘዙት በማድረግ ምን ያህል ትተጋለህ?

# ጥናት 12

## ንዑስ ርዕስ፥ የማጠቃለያ ጥናት

**ዓላማ፥**

እስካሁን “ርስትን በሰልፍ መውረስ” በሚለው ዓብይ ርዕስ ስር ያጠናናቸውን አስራ ሁለት ጥናቶች ለማጠቃለልና ለመገምገም

**መግቢያ፥** ኢያሱ 1-13 እና ዘዳ.34፥9 ይነበብ

**ጥያቄዎች፥**

1. በዚህ ዓብይ ርዕስ ከተዘጋጁት ስንቱን አጥንተሃል?
   - ያላጠናሃቸው ጥናቶች ካሉ በምን ምክንያት ነው?
2. ከተጠኑት ክፍሎች ውስጥ በቃልህ የያዝካቸው ርዕሶችና ሃሳቦች ተናገር
3. እግዚአብሄር በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ለአንተ ያዘጋጀውን ሰማያዊ ርስት ለመውረስ ከጥናቱ አንተ ምን ማድረግ እንዳለብህ ተረዳህ?
4. አሁን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ስትመለከት በሰልፍ አቅጣጫ ምን አይነት ሁኔታ ላይ ያለች ይመስልሃል? በስፋት ተወያዩበት
5. ከእነዚህ ከተጠኑት አሥራ ሁለት ጥናቶች ውስጥ ለአንተ በግልህ በተለየ መልኩ እግዚአብሔር በየትኛው ጥናት ተናግሮሃል?

ይህስ በህይወትህ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው? ተናገር?

6. ይህን ርዕስ በተመለከት ሌላ የምትለው አለህ? ሃሳብ ካለህ አካፍል።